በቤተክርስቲያን ውስጥ የመስጠት መርህ

ብዙዎቻችን አብያተክርስቲያናት፣ የቴሌቪዥን ቻናሎች እና ሌሎች መስጠት አለባችሁ አለበለዚያ ግን ከእግዚአብሔር በረከቶች ውጪ ትወድቃላችሁ ብለው ለማጭበርበር የሚሞክሩ አጋጥመውናል። ግን ያ ውሸት ነው!

ኢየሱስ ከእርሱ ቀጥሎ ገዢ አድርጎ ያስቀመጠው ገንዘብን ነው። ይህ አንድን እውነት እንድንገነዘብ የሚያደርገን ሲሆን እርሱም ገንዘብ በሰዎች የሕይወት አቅጣጫ ሁሉ ትልቅ ተጽዕኖ ያለው መሆኑን ነው።

"በአንድ ጊዜ ሁለት ጌቶችን ማገልገል የሚችል ማንም ባሪያ የለም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን ይጠጋል፤ ሌላውን ይንቃል። የእግዚአብሔርም የገንዘብም ባሪያ መሆን አትችሉም።" (ሉቃስ 16:13 NASV)

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸሎት 500 ጊዜ፣ ስለ እምነት ደግሞ 500 ጊዜ ያህል ሲጠቅስ ስለ ገንዘብ ደግሞ 2000 ጊዜ ይጠቅሳል!

ገንዘብ መገልገያችን እንጂ በራሱ የክፋት ሁሉ ሥር አይደለም። ለምን? ሐዋርያው ጳውሎስ የክፋት ሁሉ ሥር ምን እንደሆነ በግልጽ ይነግረናል።

"ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው፤ አንዳንዶች ባለጠጋ ለመሆን ካላቸው ጉጉት የተነሣ ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል፤ ራሳቸውንም በብዙ ሥቃይ ወግተዋል።" (1 ጢሞቴዎስ 6:10 NASV)

ገንዘብ መንገድ ነው እንጂ ግብ (መጨረሻ) አይደለም። ገንዘብ እኛ ግብን ወይም አቅጣጫን እውን ለማድረግ የምንጠቀምበት መሣሪያ ነው።

ሀ. የመስጠት ምሳሌዎች፦

በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስቲያን ምሳሌነት።

"ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ አደረጉ። ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ያህል ይሰጡት ነበር።" (ሐዋርያት ሥራ 2:44-45 NASV)

"ከመካከላቸውም አንድ ችግረኛ አልነበረም፤ ምክንያቱም መሬትም ሆነ ቤት የነበራቸውን ሁሉ እየሸጡ ዋጋውን አምጥተው፣ በሐዋርያት እግር ሥር በማስቀመጥ ለእያንዳንዱ በሚያስፈልገው መጠን ያካፍሉት ነበር።" (ሐዋርያት ሥራ 4:34-35 NASV)

ይህ ምንባብ የተገኘውን ገቢ በክርስቲያኖች መካከል እንደ ፍላጎታቸው እንዲካፈል መሬታቸውን፣ ቤቶቻቸውን እንኳን ሸጡ! ዛሬ ብዙዎች ለማለም ከሚመኙት እጅግ የላቀ ሰጡ!

በመቄዶንያ የነበረችው ቤተክርስቲያን ምሳሌነት።

"ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔር በመቄዶንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን ጸጋ እንድታውቁ እንፈልጋለን። የደረሰባቸው መከራ ጽኑ ቢሆንም ደስታቸው ግን የላቀ ነበር፤ ድኽነታቸው ብርቱ ቢሆንም ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር። እንደ ዐቅማቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከዐቅማቸው በላይ በፈቃዳቸው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁ። እነርሱም ቅዱሳንን ለመርዳት በሚደረገው አገልግሎት ለመሳተፍ ዕድል ያገኙ ዘንድ አጥብቀው ይለምኑን ነበር። እኛ ከጠበቅ ነው በላይ፣ በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጡ።" (2 ቆሮንቶስ 8:1-5 NASV)

እግዚአብሔር ለእኛ ገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ ገንዘብ አስፈላጊ መሆኑን ያውቃል።

"እኔ ለእናንተ ያለኝን በጎ ሐሳብ በቲቶ ልብ ውስጥ ያኖረ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፤ ... ከእርሱም ጋር በወንጌል ስብከት በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን ወንድም ልከነዋል። ከዚህም በላይ ስጦታውን በምንወስድበት ጊዜ አብሮን እንዲሄድ በአብያተ ክርስቲያናት ተመርጦአል፤ ስጦታውንም የምንወስደው ጌታን ራሱን ለማክበርና ሌሎችን ለመርዳት ካለን በጎ ፈቃድ የተነሣ ነው። በዚህ በምናከናውነው የቸርነት ሥራ አንዳች ነቀፋ እንዳይገኝብን እንጠነቀቃለን።" (2 ቆሮንቶስ 8:16፤ 18-20 NASV)

ለ. የእግዚአብሔር ጸጋ ሲገናኝን፦

በልዩነት እንራመዳለን።

"ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ገብቶ በዚያ አልፎ ይሄድ ነበር። ስሙ ዘኬዎስ የተባለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፤ ዋና ቀረጥ ሰብሳቢና ሀብታም ነበረ። እርሱም ኢየሱስ የተባለው የትኛው እንደሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱ አጭር ነበረና ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሊያየው አልቻለም። ኢየሱስ በዚያ መንገድ ያልፍ ስለ ነበርም፣ ሊያየው ወደ ፊት ሮጦ አንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ። ኢየሱስም እዚያ ቦታ ሲደርስ፣ ቀና ብሎ፣ ዘኬዎስ ሆይ፤ ዛሬ አንተ ቤት መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው። እርሱም ፈጥኖ ወርዶ በደስታ ተቀበለው። በዚያ የነበሩ ሰዎችም ይህንን አይተው፣ ከኀጢአተኛ ቤት ገብቶ ሊስተናገድ ነው። በማለት ሁሉም ማጕረምረም ጀመሩ። ዘኬዎስ ግን ቆመና ጌታን፣ ጌታ ሆይ፤ እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ ግማሹን ለድኾች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ቀምቼ ከሆነ፣ አራት ዕጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ” አለው። ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ ይህ ሰው ደግሞ የአብርሃም ልጅ ስለ ሆነ፣ ዛሬ መዳን ወደዚህ ቤት መጥቶአል፤" (ሉቃስ 19:1-9 NASV)

ኢየሱስ ታዋቂ ሰው ከሆነው ዘኬዎስ ጋር በነበረበት ጊዜ ኢየሱስ "የአብርሃም ልጅ" በማለት ይጠራዋል፤ ከኃጢአተኛ አኗኗሩ የተነሳ ዘኬዎስ ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው በሚቆጥሩት ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም።

ኢየሱስ ለዘኬዎስ ገደብ የለሽ ጸጋውን (ፍቅሩን) አፈሰሰ፤ ዘኬዎስም ይህ ጸጋ (ፍቅር) እንዲያቅፈው ሲፈቅድ እውነተኛ ንስሃ ወደ ልቡ መጣ።

አስታውሱ! ኢየሱስ ለዘኬዎስ አንድም ትእዛዝ አልሰጠውም። ሆኖም የኢየሱስ ጸጋ (ፍቅር) ልቡን በሚነካበት ጊዜ የሀብቱን ግማሽ ለድሆች ለመስጠት እና ለሰረቀው ለእያንዳንዱን ሰው ሁሉ አራት እጥፍ ለመክፈል ፈለገ። አያችሁ! የኢየሱስ ፍቅር በመጣ ጊዜ የገንዘብ ፍቅር ሞተ።

ሁኔታው ምንም ይሁን ምን በታማኝነት እንሰጣለን።

"የደረሰባቸው መከራ ጽኑ ቢሆንም ደስታቸው ግን የላቀ ነበር፤ ድኽነታቸው ብርቱ ቢሆንም ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር።" (2 ቆሮንቶስ 8:2 NASV)

ጳውሎስ ለቆሮንጦስ ሰዎች የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩበት ሁኔታ (የድህነት ጥልቀት) ሳያግዳቸው ከአቅማቸው በላይ እንዴት እንደሰጡ ይነግራቸዋል።

ሐ. ለምን እንሰጣለን?

እራሳችንን ማቅረባችንን ለማሳየት።

"እነርሱም ቅዱሳንን ለመርዳት በሚደረገው አገልግሎት ለመሳተፍ ዕድል ያገኙ ዘንድ አጥብቀው ይለምኑን ነበር። እኛ ከጠበቅ ነው በላይ፣ በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጡ።" (2 ቆሮንቶስ 8:4-5 NASV)

በመስጠት ፍቅራችንን በተግባር ለማሳየት።

"ይህን የምለው ትእዛዝ ለመስጠት ብዬ አይደለም፤ ነገር ግን ሌሎች ከሚያሳዩት ትጋት አንጻር የፍቅራችሁን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ነው። የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና፤ በእርሱ ድኽነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ሀብታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል ድኻ ሆነ።" (2 ቆሮንቶስ 8:8-9 NASV)

መስጠት በአዲስ ኪዳን እውነተኛ ፍቅራችንን ለማሳየት ነው። ትዕዛዝ አይደለም። ምን ያህል ጊዜ፣ ምን ያህል መጠን ሠጠህ ሣይሆን ምን ያህል ፍቅር አለህ ነው።

ስንሰጥ ምላሽ ፈልገን፣ ጠብቀን (አንድ ሺህ ሰጠን አሥር ሺህ) መሆን የለብንም።

በመስጠት ውሳኔያችንን በተግባር ለማሳየት።

"ስለዚህ ጒዳይ የምሰጣችሁ ጠቃሚ ምክር ይህ ነው፤ ባለፈው ዓመት በመስጠት ብቻ ሳይሆን ለመስጠት በማሰብም ቀዳሚ ነበራችሁ፤ አሁንም የጀመራችሁትን ተግባር በዐቅማችሁ መጠን ከፍጻሜ አድርሱት፤ ይህም ለመስጠት የነበራችሁ በጎ ፈቃድ እውን እንዲሆን ነው።" (2 ቆሮንቶስ 8:10-11 NASV)

መ. የምንሰጠው እንዴት ነው?

በነፃ ፈቃዳችን፦ መስጠት ግዳጅ ሳይሆን ዕድል ስለሆነ ነው።

"እንደ ዐቅማቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከዐቅማቸው በላይ በፈቃዳቸው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁ። እነርሱም ቅዱሳንን ለመርዳት በሚደረገው አገልግሎት ለመሳተፍ ዕድል ያገኙ ዘንድ አጥብቀው ይለምኑን ነበር።" (2 ቆሮንቶስ 8:3-4 NASV)

የመስጠት ግፊት ወይም ፍላጎት እንዲሰማን እግዚአብሔር አይፈልግም።

በደስታ መስጠት፦ በግዳጅ ማድረግ ሳይሆን እግዚአብሔር ባሳየን ጸጋ እና ምህረት መስጠት ስለፈለግን ነው።

"እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይሆን፣ በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል።" (2 ቆሮንቶስ 9:7 NASV)

እግዚአብሔር በግዴታ ሳይሆን በደስታ እንድንሰጥ ይፈልጋል። ለምን? በአዲሱ ኪዳን ስር የመስጠት ዓላማ ደስተኛ ልብ ነውና!

በመስዋእትነት መስጠት፦ በስስት ወይም በተሳሳተ ዓላማ ሳይሆን በልግስና፣ ሀላፊነት የጎደለው ወይም ከእውነታው የራቀ ሳንሆን የምንችለውን ያህል።

"እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይሆን፣ በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል።" (2 ቆሮንቶስ 9:7 NASV)

አስበንበት መስጠት፦ ይህ በድንገት ወይም በአጋጣሚ ሳይሆን በደንብ አቅደንበት መስጠት ነው።

"ለቅዱሳን ስለሚደረገው አገልግሎት ልጽፍላችሁ አያስፈልግም። ምክንያቱም ሌሎችን ለመርዳት ያላችሁ በጎ ፈቃድ ዐውቃለሁ፤ ካለፈው ዓመት ጀምሮ እናንተ በአካይያ የምትኖሩ ሌሎችን ለመርዳት ዝግጁ እንደሆናችሁ ለመቄዶንያ ሰዎች አፌን ሞልቼ ተናግሬአለሁ፤ ቅን ፍላጎታችሁም ብዙዎችን ለበጎ ስራ አነሣሥቶአል። እንግዲህ በዚህ ነገር በእናንተ ላይ ያለን ትምክሕት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር አስቀድሞ ስለ እናንተ እንደ ተናገርሁት ተዘጋጅታችሁ እንድትገኙ ወንድሞችን ልኬአለሁ። ምናልባት የመቄዶንያ ሰዎች ከእኔ ጋር መጥተው ሳትዘጋጁ ቢያገኟችሁ፣ እናንተ ብቻ ሳትሆኑ እኛም ያን ያህል በእናንተ በመመካታችን እናፍራለን። ስለዚህ ወንድሞች አስቀድመው ወደ እናንተ እንዲመጡና ከዚህ በፊት ለመስጠት ቃል የገባችሁትን ስጦታ

አጠናቃችሁ እንድትጠብቋቸው፣ እነርሱን መለመን አስፈላጊ ሆኖ አግኝቻለሁ፤ እንግዲህ በልግስና ለመስጠት ያሰባችሁት ነገር በግዴታ ሳይሆን በፈቃደኝነት የተዘጋጀ ይሆናል።" (2 ቆሮንቶስ 9፡1-5 NASV)

በልግስና መስጠት፦ ሌሎች ሰዎችን ለመርዳት እግዚአብሔርን ለማመስገን ምክንያት እንዲሆናቸው መስጠት ነው።

"ለዘሪ ዘርን፣ ለመብላት እንጀራን የሚሰጥ እርሱ የምትዘሩትን አትረፍርፎ ይሰጣችኋል፤ የጽድቃችሁንም ፍሬ ያበዛላችኋል። ሁልጊዜ በልግስና መስጠት እንድትችሉ በሁሉ ነገር ያበለጽጋችኋል፤ ልግስናችሁም በእኛ በኩል የሚደርሳቸው ሰዎች እግዚአብሔርን ለማመስገን ምክንያት ይሆናቸዋል።" (2 ቆሮንቶስ 9:10-11 NASV)

“ይህ የምትሰጡት አገልግሎት የቅዱሳንን ጕድለት የሚያሟላ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ነው። የክርስቶስን ወንጌል ተቀብላችሁ ስለ ታዘዛችሁና ለእነርሱም ሆነ ለሌሎች ስላሳያችሁት ልግስና ሰዎች ተፈትኖ ስላለፈው አገልግሎታችሁ እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤ ስለ እናንተም በሚጸልዩበት ጊዜ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ታላቅ ጸጋ የተነሣ ይናፍቋችኋል።" (2 ቆሮንቶስ 9:12-14 NASV)

በመጋቢ አለማየሁ ገመቹ ተዘጋጀ

በዕትመት አዘጋጅቶ ለሽያጭ ማዋል የተከለከለ ነው!

ነሐሴ 4/12/2014 ዓ.ም